# መጽሐፈ አስቴር

## ንግሥት አስጢን ከክብሯ ወረደች

1 ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ
ያሉትን አንድ መቶ ሃያ ሰባት አገሮች
ይገዛ በነበረው በጠረክሲስ ዘመነ መንግ
ሥት እንዲህ ሆነ፤ 2በዚያን ዘመን ንጉሡ
ጠረክሲስ የገዛው በሱሳ ግንብ ባለው ንጉ
ሣዊ ዙፋኑ ሆኖ ነበር:: 3እርሱም በነገሠ
በሦስተኛው ዓመት ለመኳንንቱና ለሹማ
ምቱ ሁሉ ታላቅ ግብዣ አደረገ:: በግብ
ዣውም የፋርስና የሜዶን የጦር አዛዦች፣
መሳፍንትና የየአውራጃው መኳንንት ተገኝ
ተው ነበር::
4ለእነርሱም የመንግሥቱን ሰፊ ሀብት፣
የግርማውን ታላቅነትና ክብር አንድ መቶ
ሰማንያ ቀን ሙሉ አሳያቸው:: 5እነዚህ
ቀናት ካለፉ በኋላ፣ ንጉሡ በሱሳ ግንብ
ለነበሩት፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ ላለው
ሕዝብ ሁሉ፣ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ
ዙሪያውን በአትክልት በተከበበው አደባባይ
ሰባት ቀን የፈጀ ግብዣ አደረገ:: 6አደባባ
ዩም ከነጭና ከሰማያዊ በፍታ የተሠሩ መጋ
ረጃዎች ነበሩት፤ እነርሱም የብር ቀለበት
በተበጀላቸው፣ ከነጭ በፍታና ከሐምራዊ
ቀለም በተሠሩ ገመዶች በዕብነ በረዱ
ምሰሶዎች ላይ ተንጠልጥለው ነበር:: ነጭና
ቀይ ቀለማት ተሰበጣጥረው በተነጠፉበት
ወለል ላይ የወርቅና የብር ድንክ ዐልጋ
ዎች ነበሩ፤ እነርሱም ከዕብነ በረድ፣ ቀስተ
ደመና ከሚመስሉ ቀለሞችና ከሌሎች
የከበሩ ድንጋዮች የተሠሩ ነበሩ:: 7የወ
ይን ጠጁም አንዱ ከሌላው ልዩ በሆነ
የወርቅ ዋንጫ ይቀርብ ነበር፤ ከንጉሡም
ልግስና የተነሣ የቤተ መንግሥቱ የወይን
ጠጅ የተትረፈረፈ ነበር:: 8ንጉሡ ለእያን
ዳንዱ ሰው የሚፈልገውን ያህል እንዲያ
ቀርቡለት የወይን ጠጅ አሳላፊዎቹን ሁሉ
አዝዞ ስለ ነበረ፣ በንጉሡ ትእዛዝ መሠረት
እያንዳንዱ ተስተናጋጅ እንዲጠጣ ተፈቅዶ
ለት ነበር::
9ንግሥት አስጢንም በንጉሥ ጠረክሲስ
ቤተ መንግሥት እንደዚሁ ለሴቶች ግብዣ
አድርጋ ነበር::
10በሰባተኛው ቀን ንጉሥ ጠረክሲስ ከወ
ይን ጠጁ የተነሣ ደስ ስለ ተሰኘ፣ አገልጋ
ዮቹ የሆኑትን ሰባቱን ጃንደረቦች ምሁ
ማንን፣ ባዛንን፣ ሐርቦናን፣ ገበታን፣ ዘቶል
ያንን፣ ዜታርንና ከርከስን እንዲህ ብሎ
አዘዛቸው፤ 11ይኸውም ንግሥት አስጢን
የደስ ደስ ያላት ነበረችና ውበቷ ለሕዝ
ቡና ለመኳንንቱ እንዲታይ ዘውዷን ጭና
ንጉሡ ፊት እንዲያመጧት ነበር:: 12አገል
ጋዮቹ የንጉሡን ትእዛዝ በነገሯት ጊዜ ግን፣
ንግሥት አስጢን መሄድ አልፈለገችም:: ከዚ
ያም ንጉሡ በጣም ተቈጣ፤ እጅግም ተና
ደደ::
13ሕግንና ፍትሕን በተመለከተ የሊቃው
ንቱን ምክር መጠየቅ በንጉሥ ዘንድ የተ
ለመደ ነበርና፣ ስለ ዘመናት ሁኔታ ዕው
ቀት ካላቸው ጠቢባን ጋር ተነጋገረበት፤
14እነዚህ አርቄስዮስ፣ ሼታር፣ አድማታ፣
ተርሺሽ፣ ሜሬስ፣ ማሌሴዓር፣ ምሙካ
የተባሉ ሰባቱ የፋርስና የሜዶን መኳንንት
በንጉሡ ዘንድ የተለየ ስፍራና በመንግሥ
ቱም አመራር ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያላቸው
ነበሩ::
15ንጉሡም፣ “በጃንደረቦቹ በኩል የተ
ላከባትን የንጉሥ ጠረክሲስን ትእዛዝ ስላ
ልፈጸመች፣ በሕጉ መሠረት በንግሥት አስ
ጢን ላይ ምን መደረግ አለበት?” ሲል ጠየ
ቃቸው::
16ከዚያም ምሙካ በንጉሡና በመኳንንቱ
ፊት እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ንግሥት አስ
ጢን የበደለችው ንጉሡን ብቻ ሳይሆን፣
መኳንንቱን ሁሉና በመላው የንጉሥ ጠረ
ክሲስ አውራጃዎች የሚኖሩትን ሕዝቦች
ጭምር ነው:: 17ይህ የንግሥቲቱ አድራ
ጎት በሌሎቹ ሁሉ ዘንድ ስለሚሰማ፣ ባሎ
ቻቸውን ይንቃሉ፤ ‘ንጉሥ ጠረክሲስ ንግ
ሥት አስጢን ወደ እርሱ እንድትመጣ ቢያ
ዛትም፣ እርሷ ግን መሄድ አልፈለገችም’
ይላሉ:: 18በዚህች በዛሬዪቱም ዕለት የንግ
ሥቲቱን አድራጎት የሰሙ የፋርስና የሜ
ዶን መኳንንት ሚስቶች፣ ለንጉሡ መኳን
ንት ሁሉ በዚሁ ዐይነት ሊመልሱ ነው፤
እንዲህ ከሆነ ደግሞ ማብቂያ የሌለው ንቀ
ትና ጠብ ይፈጠራል::
19“ስለዚህ ነገሩ ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው
ከሆነ፣ አስጢን ወደ ንጉሡ ወደ ጠረክሲስ
ዘንድ ከእንግዲህ ወዲህ ፈጽሞ እንዳትገባ
ንጉሣዊ ዐዋጅ ይውጣ፤ ይህም የማይሻር
ሆኖ በፋርስና በሜዶን ሕጎች ይጻፍ፤ እን
ዲሁም ንጉሡ የእቴጌነቷን ክብር ከእርሷ
ለምትሻል ለሌላዪቱ ይስጥ:: 20ከዚያም የን
ጉሡ ዐዋጅ በሰፊው ግዛቱ ሁሉ ሲነገር፣
ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉት ሴቶች ሁሉ
ባሎቻቸውን ያከብራሉ::”

1፥1 ዕዝ4፥6፤ አስ8፥9፤9፥30፤ ዳን3፥2፤ 6፥1
1፥2 ዕዝ4፥9፤ አስ2፥8
1፥3 1ነገ3፥15
1፥5 መሳ14፥17፤ 2ነገ21፥18
1፥6 አስ7፥8፤ ሕዝ 23፥41፤ አሞ3፥12፤6፥4
1፥7 አስ2፥18፤ ዳን5፥2
1፥9 1ነገ3፥15
1፥10 ዘፍ14፥18፤ መሳ16፥25፤ ሩት3፥7፤አስ3፥15፤ 5፥6፤7፥2፤ ምሳ31፥4-7፤ ዳን5፥1-4
1፥11 መዝ45፥11፤ ማሕ2፥4፤ሕዝ16፥14
1፥12 ዘፍ39፥19፤ ኣስ2፥21፤7፥7፤ ምሳ19፥12
1፥13 1ዜና12፥32
1፥14 አስ7፥14
1፥18 ምሳ19፥13፤ 27፥15
1፥19 አስ8፥8፤ መክ8፥4፤ ዳን6፥8፡12

21ንጉሡና መኳንንቱ ሁሉ በዚህ ምክር ተደሰቱ፤ ንጉሡም ምሙካ ያቀረበውን ሐሳብ በሥራ ላይ አዋለው። 22እያንዳንዱ ሰው በራሱ ቤተ ሰብ ላይ ገዥ እንዲሆን መልእክት አስተላለፈ፤ መልእክቱም ለየአውራጃዎቹ በየራሳቸው ጽሑፍና ለእያንዳንዱ ሕዝብ በየራሱ ቋንቋ ተጽፎ በግዛቱ ሁሉ ተበተነ።

### አስቴር ንግሥት ሆነች

**2** ከዚህ በኋላ ንጉሡ ጠረክሲስ ቍጣው ሲበርድለት አስጢንን፣ ያደረገችውን ነገርና በእርሷም ላይ ያስተላለፈውን ዐዋጅ ዐሰበ። 2ከዚያም የንጉሡ የቅርብ አገልጋዮች እንዲህ የሚል ሐሳብ አቀረቡ፤ “ለንጉሡ ቈንጆ ልጃገረዶች ይፈለጉለት፤ 3እነዚህን ሁሉ ቈንጆ ልጃገረዶች በሱሳ ግንብ ወደሚገኘው ልዩ የሴቶች መኖሪያ ቦታ እንዲያመጡ፣ ንጉሡ በግዛቱ በሚገኙት አውራጃዎቹ ሁሉ ባለሥልጣኖችን ይሹም፤ እነርሱም የሴቶች የበላይ ኀላፊ በሆነው በንጉሡ ጃንደረባ በሄጌ ኀላፊነት ሥር ይሁኑ፤ የውበትም እንክብካቤ ይደረግላቸው። 4ከዚያም ንጉሡን ደስ የምታሰኘው ልጃገረድ በአስጢን ፈንታ ንግሥት ትሁን።” ምክሩ ንጉሡን ደስ አሰኘው፤ በተባለውም መሠረት አደረገ።

5በዚህ ጊዜ ከብንያም ነገድ የቂስ ልጅ፣ የሰሜኢ ልጅ፣ የኢያዕር ልጅ መርዶክዮስ የሚባል አንድ አይሁዳዊ በሱሳ ግንብ ይኖር ነበር፤ 6እርሱም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ከማረካቸው ከይሁዳ ንጉሥ ከኢኮንያን[ሀ] ጋር ከኢየሩሳሌም በምርኮ ከተወሰዱት አንዱ ነበር። 7መርዶክዮስ አንዲት ሀደሳ የምትባል የአጎቱ ልጅ ነበረችው፤ አባትና እናት ስላልነበራት፣ ያሳደጋት እርሱ ነበር። አስቴር ተብላ የምትጠራው ይህች ልጃገረድ በተክለ ሰውነቷም ሆነ በመልኳ እጅግ ውብ ነበረች። አባቷና እናቷ ከሞቱ በኋላ መርዶክዮስ እንደ ራሱ ልጅ አድርጎ ወሰዳት።

8የንጉሡ ትእዛዝና ዐዋጅ በወጣ ጊዜ፣ ብዙ ልጃገረዶች ወደ ሱሳ ግንብ ተወሰደው ለጠባቂው ለሄጌ ተሰጡ፤ አስቴርም ወደ ንጉሡ ቤተ መንግሥት ተወስዳ፣ ለሴቶቹ ጠባቂ ለሄጌ በዐደራ ተሰጠች። 9ልጃገረዲቱም ደስ አሰኘችው፤ በእርሱም ዘንድ መወደድን አተረፈች፤ እርሱም የውበት መንከባከቢያዋንና የተለየ ምግብ ወዲያውኑ ሰጣት። ከቤተ መንግሥቱ የተመረጡ ሰባት ደንገጡሮችን በመመደብም እርሷንና ደንገጡሮቿን ምርጥ ወደ ሆነው የሴቶች መጠበቂያ አዛወረ።

10መርዶክዮስ እንዳትናገር አዞአት ስለ ነበር፣ አስቴር የየት አገር ሰውና የእነማን ወገን እንደ ሆነች አልገለጸችም። 11መርዶክዮስም አስቴር እንዴት እንደ ሆነችና ምንስ እንዳጋጠማት ለማወቅ፣ በየዕለቱ በሴቶች መጠበቂያ አደባባይ አጠገብ ወዲያና ወዲህ ይመላለስ ነበር።

12አንዲት ልጃገረድ ወደ ንጉሥ ጠረክሲስ ዘንድ ለመግባት ተራዋ ከመድረሱ በፊት ስድስት ወር በከርቤ ዘይት፣ ስድስት ወር ደግሞ ልዩ ልዩ ሽቱ በመቀባትና በተለያዩ የፊት ቀለሞች በመዋብ ባጠቃላይ ዐሥራ ሁለት ወር መቈየት ነበረባት፤ 13ወደ ንጉሡ ዘንድ የምትገባውም በዚህ ሁኔታ ሲሆን፣ ሴቶቹ ከሚኖሩበት ስፍራ ወደ ንጉሡ ቤተ መንግሥት ስትሄድ፣ መውሰድ የምትፈልገው ማናቸውም ነገር ይሰጣት ነበር። 14ሲመሽ ወደዚያው ትሄዳለች፤ ሲነጋም የቁባቶች ኀላፊ በሆነው በንጉሡ ጃንደረባ በሻአሽጋዝ ጥበቃ ሥር ወደሚገኘው ወደ ሌላው የሴቶች መጠበቂያ ቤት ትመለሳለች፤ ደስ የተሰኘባት ካልሆነችና በስሟ ካልጠራት ዳግመኛ ወደ ንጉሡ ዘንድ አትገባም።

15መርዶክዮስ እንደ ልጁ አድርጎ ያሳደጋት የአጎቱ የአቢካኢል ልጅ አስቴር ወደ ንጉሡ ዘንድ የምትሄድበት ተራ በደረሰ ጊዜ የሴቶች ልዩ ጥበቃ ቤት ኀላፊ የሆነው ሄጌ የነገራትን እንጂ፣ ሌላ ምንም አልጠየቀችም። አስቴር በሚያዩዋት ሁሉ ዘንድ ሞገስ አገኘች። 16በነገሠ በሰባተኛው ዓመት ቴቤት በተባለው በዐሥረኛው ወር ወደ ንጉሥ ጠረክሲስ ቤተ መንግሥት ተወሰደች።

17በዚህ ጊዜ ንጉሡ ከሌሎቹ ሴቶች ሁሉ ይበልጥ አስቴርን ወደዳት፤ ከሌሎቹ ደናግልም ሁሉ ይልቅ በእርሱ ዘንድ ሞገስንና መወደድን አገኘች። ስለዚህ የእቴጌነት ዘውድ በራሷ ላይ ጫነላት፤ በአስጢንም ፈንታ ንግሥት አደረጋት። 18ንጉሡም ስለ አስቴር ክብር ለመኳንንቱና ለሹማምቱ ሁሉ ታላቅ ግብዣ አደረገ፤ በዓሉም በየአውራጃዎቹ ሁሉ እንዲከበር ዐወጀ፤ በንጉሣዊ ልግስናውም ስጦታ አደረገ።

### መርዶክዮስ በንጉሡ ላይ የተጠነሰሰውን ሤራ ደረሰበት

19ደናግሉ ለሁለተኛ ጊዜ ተሰብስበው ሳለ፣ መርዶክዮስ በንጉሡ በር ተቀምጦ ነበር። 20አስቴር ግን ልክ መርዶክዮስ እንደ ነገራት የማን ወገንና የየት አገር ሰው እንደ ሆነች ደብቃ ነበር፤ ይህ የሆነበት ምክንያት መርዶክዮስ በሚያሳድጋት ጊዜ ታደ

1፥22 ነህ13፥24
2፥1 አስ7፥10
2፥5 1ሳሙ9፥1
2፥6 2ነገ24፥15፤ ዳን1፥1-5፤5፥13
2፥7 ዘፍ39፥6፤ 41፥45
2፥8 ነህ1፥1፤ አስ1፥2፤ዳን8፥2
2፥9 ዘፍ37፥3፤ 39፥21፤ 1ሳሙ9፥22-24 2ነገ25፥30፤ አስ 9፥19፤ ሕዝ16፥9-13፤ ዳን1፥5
2፥10 ቍ20
2፥12 ምሳ27፥9፤ መሓ1፥3፤ኢሳ3፥24
2፥14 1ነገ11፥3፤ አስ4፥11፤መሓ6፥8፤ ዳን5፥2
2፥15 ዘፍ18፥3፤ 30፥27፤አስ5፥8፤7፥3፤ 8፥5፤9፥29፤ መዝ 45፥14
2፥17 ሕዝ16፥9-13
2፥18 ዘፍ40፥20፤ 1ነገ3፥15፤አስ1፥7
2፥19 አስ4፥2፤5፥13
2፥20 ቍ10

ሀ6 በዕብራይስጥ፣ *ኢኮንያን* የሚለው ስም *ኢዮአቄም* ከሚለው ጋር አንድ ዐይነት ነው።

ርግ እንደ ነበረው ሁሉ፣ አሁንም ምክሩን
ትከተል ስለ ነበር ነው።
21መርዶክዮስ በንጉሡ በር ተቀምጦ
ሳለ፣ በሩን ከሚጠብቁት ከንጉሡ የጦር
አለቆች ሁለቱ ገበታና ታራ ተቈጡ፤ ንጉሥ
ጠረክሲስንም ለመግደል ዶለቱ። 22መር
ዶክዮስም አድማውን ስለ ደረሰበት፣ ለንግ
ሥት አስቴር ገለጠላት፤ እርሷም ይህን
ከመርዶክዮስ ማግኘቷን ለንጉሡ ገልጣ
ነገረችው። 23ነገሩ ሲጣራም እውነት ሆኖ
ተገኘ፤ ሁለቱም ሹማምት በስቅላት ሞት
ተቀጡ። ይህ ሁሉ በንጉሡ ፊት በታሪክ
መዝገብ ተጻፈ።

## ሐማ አይሁድን ለማጥፋት የሸረበው ሤራ

3 ከዚህም ነገር በኋላ ንጉሥ ጠረክሲስ
የአጋጋዊውን የሐመዳቱን ልጅ ሐማን
ከፍ ከፍ አደረገው፤ ከሌሎቹም መኳንንት
ሁሉ ከፍተኛውን ሥልጣን በመስጠት አከበ
ረው። 2ንጉሡ ስለ እርሱ ይህ እንዲደረ
ግለት አዞ ስለ ነበር፣ በንጉሡ በር ያሉት
የመንግሥቱ ሹማምት ሁሉ ለሐማ ተንበ
ርክከው እጅ በመንሣት አክብሮታቸውን
ይገልጡለት ነበር። መርዶክዮስ ግን ወድቆ
አልሰገደለትም፤ አክብሮትም አላሳየውም።
3ታዲያ በንጉሡ በር ያሉት የንጉሡ
አገልጋዮች መርዶክዮስን፣ “የንጉሡን ትእ
ዛዝ ለምን ትተላለፋለህ?” ሲሉ ጠየቁት።
4ይህንንም በየቀኑ ይነግሩት ነበር፤ እርሱ
ግን አልተቀበላቸውም። አይሁዳዊ መሆኑን
ነግሮአቸው ስለ ነበር፣ የመርዶክዮስ ባሕ
ርይ እስከ መቼ ሊቀጥል እንደሚችል ለማ
የት ሲሉ ይህንኑ ለሐማ ነገሩት።
5ሐማም መርዶክዮስ ወድቆ እንዳልሰገደ
ለትና እንዳላከበረው ሲያይ እጅግ ተቈጣ።
6ይልቁንም መርዶክዮስ ከእነማን ወገን መሆ
ኑን በተረዳ ጊዜ፣ መርዶክዮስን ብቻ መግ
ደል እንደ ኢምንት ቈጠረው፤ ስለዚህ ሐማ
በመላው የጠረክሲስ መንግሥት ውስጥ
የሚገኙትንና የመርዶክዮስ ወገን የሆኑትን
አይሁድ ሁሉ ለማጥፋት ዘዴ ፈለገ።
7ንጉሥ ጠረክሲስ በነገሠ በዐሥራ ሁለ
ተኛው ዓመት ኒሳን በተባለው በመጀመሪ
ያው ወር፣ ቀኑንና ወሩን ለመለየት ፉር
የተባለ ዕጣ ሐማ ባለበት ጣሉ፤ ዕጣውም
አዳር በተባለው በዐሥራ ሁለተኛው ወር
ላይ ወደቀ።
8ከዚያም ሐማ ንጉሥ ጠረክሲስን እንዲህ
አለው፤ “በአሕዛብ መካከል በመንግሥትህ
አውራጃዎች ሁሉ ተሠራጭቶና ተበታትኖ
የሚኖር አንድ ሕዝብ አለ፤ ይህም ሕዝብ
ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ የተለየ ልማድ ያለ
ውና የንጉሡንም ሕግ የማይታዘዝ ነው፤
ታዲያ ይህን ሕዝብ ዝም ማለቱ ለንጉሡ
አይበጅም። 9ነገሩ ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው
ከሆነ፣ እነርሱን ለማጥፋት ዐዋጅ ይውጣ፤
እኔም ይህን ተግባር ለሚፈጽሙ ሰዎች
የሚውል ዐሥር ሺህ መክሊት ብር ወደ
መንግሥት ግምጃ ቤት አስገባለሁ።”
10ስለዚህ ንጉሡ የቀለበት ማኅተሙን ከጣቱ
አውልቆ የአይሁድ ጠላት ለሆነው ለአጋ
ጋዊው ለሐማዳቱ ልጅ ለሐማ ሰጠው።
11ንጉሡም ሐማን፣ “ገንዘቡን እዚያው ያዘው፤
ሕዝቡንም እንዳሻህ አድርገው” አለው።
12ከዚያም በመጀመሪያው ወር ዐሥራ
ሦስተኛው ቀን የንጉሡ ጸሓፊዎች ተጠሩ።
እነርሱም የሐማን ትእዛዝ በሙሉ በየአውራ
ጃው ፊደልና በየሕዝቡ ቋንቋ፣ ለንጉሡ
እንደራሴዎች፣ ለልዩ ልዩ አውራጃ ገዦችና
ለልዩ ልዩ ሕዝቦች መኳንንት ጻፉ። ይህም
የተጻፈው በራሱ በንጉሡ ጠረክሲስ ስም
ሲሆን፣ የታተመውም በራሱ ማኅተም ነበር።
13አዳር በተባለው በዐሥራ ሁለተኛው ወር፣
በዐሥራ ሦስተኛው ቀን ወጣት፣ ሽማግሌ፣
ሴትና ሕፃን ሳይባል አይሁድ ሁሉ በዚ
ያኑ ዕለት እንዲጠፉ፣ እንዲገደሉና እንዲ
ደመሰሱ፣ ሀብታቸውም እንዲዘረፍ ደብዳቤ
ለንጉሡ አውራጃዎች ሁሉ በመልእክተኞች
እጅ ተላከ። 14ለእያንዳንዱም አውራጃ ሕዝብ
እንዲታወቅ፣ እነርሱም ለዚያ ቀን ዝግጁ
እንዲሆኑ፣ የዋናው ዐዋጅ ቅጅ ሕግ እን
ዲወጣና ወደ እያንዳንዱም አውራጃ እን
ዲላክ ተደረገ።
15መልእክተኞቹ በንጉሡ ትእዛዝ ተቻ
ኰለው ወጡ፤ ዐዋጁም በሱሳ ግንብ ተላ
ለፈ። ንጉሡና ሐማ ለመጠጣት ተቀ
መጡ፤ የሱሳ ከተማ ግን ግራ ተጋብታ
ነበር።

## መርዶክዮስ የአስቴርን ርዳታ ጠየቀ

4 መርዶክዮስ የተደረገውን ሁሉ ባወቀ
ጊዜ፣ ልብሱን ቀደደ፤ ከዚያም ማቅ
ለብሶ፣ በራሱ ላይ ዐመድ ነስንሶ ድምፁን
ከፍ በማድረግ አምርሮ እየጮኸ ወደ
ከተማዪቱ መካከል ወጣ። 2ማቅ የለበሰ
እንዲገባ ስለማይፈቀድለት፣ የሄደው እስከ
ንጉሡ በር ድረስ ብቻ ነበር። 3የንጉሡ ዐዋ
ጅና ትእዛዝ በደረሰበት አውራጃ ሁሉ፣
በአይሁድ መካከል ታላቅ ሐዘን ሆነ፤ ጾሙ፤
አለቀሱ፤ ጮኹም። ብዙዎቹም ማቅና ዐመድ
ላይ ተኙ።
4የአስቴር ደንገጡሮችና ጃንደረቦች
መጥተው ስለ መርዶክዮስ በነገሯት ጊዜ፣
እጅግ አዘነች፤ እርሷም በማቁ ፈንታ የሚለ
ብሰውን ልብስ ላከችለት፤ እርሱ ግን አል
ተቀበላቸውም። 5ከዚያም አስቴር ከንጉሡ

2፥21 ዘፍ40፥2፤ አስ1፥12፤3፥5፤ 5፥9፤ 7፥7
2፥23 ዘፍ40፥19፤ ዘዳ21፥22-23፤ አስ 6፥1፤10፥2፤ 6፥2፤መዝ7፥14-16፤ ምሳ 26፥27፤ መክ10፥8
3፥1 ዘፀ17፥8-16፤ ዘኁ24፥7፤ ዘዳ25፥17-19፤ 1ሳሙ14፥48
3፥3 አስ5፥9፤ ዳን3፥12
3፥4 ዘፍ39፥10
2፥5 አስ2፥21
3፥6 አስ9፥24፤ መዝ 74፥8፤83፥4፤ ምሳ 16፥25
3፥7 ቍ13፤ ዘሌ 16፥8፤ 1ሳሙ10፥21፤ አስ9፥24፡26፤9፥19
3፥8 ዕዝ4፥15፤ ኤር29፥7፤ዳን6፥13፤ ሐሥ 16፥20-21
3፥9 አስ7፥4
3፥10 ዘፍ41፥42
3፥12 ዘፍ38፥18፤ ነህ13፥24
3፥13 ቍ7፤ 1ሳሙ 15፥3፤ ዕዝ4፥6፤ አስ8፥11፤9፥10
3፥14 አስ8፥8፤9፥1
3፥15 አስ1፥10፤ 8፥14፡15
4፥1 ዘፀ11፥6፤ ዘኁ14፥6፤ 2ሳሙ 13፥19፤ መዝ30፥11፤ ሕዝ27፥30-31
4፥2 አስ2፥19

ጃንደረቦች መካከል እርሷን እንዲያገለ
ግል የተመደበውን ሀታክን ጠርታ፣ መርዶ
ክዮስ ምን ችግር እንደ ገጠመውና ስለ
ምንስ እንደዚህ እንደ ሆነ እንዲያጣራ
ላከችው፡፡
6ስለዚህ ሀታክ በንጉሡ በር ፊት ለፊት
ወደሚገኘው ወደ ከተማዪቱ አደባባይ
ወደ መርዶክዮስ ወጣ፡፡ 7መርዶክዮስ የደረ
ሰበትን ነገር ሁሉ፣ እንዲሁም ሐማ የአይ
ሁድን ሕዝብ ለማጥፋት ወደ ንጉሡ
ግምጃ ቤት ለማግባት ቃል የገባውን የገ
ንዘብ ልክ ጭምር ነገረው፡፡ 8አይሁድን ለማ
ጥፋት በሱሳ የወጣውን የዋናውን ዐዋጅ
ቅጅም ለአስቴር እንዲያሳያትና በዝርዝር እን
ዲያስረዳት ሰጠው፤ ወደ ንጉሡም ዘንድ
ገብታ ስለ ሕዝቧ ምሕረት እንድትጠይቅና
እንድትማልድ አጥብቆ ይነግራት ዘንድ
አሳሰበው፡፡
9ሀታክም ተመልሶ መርዶክዮስ የነገረ
ውን ሁሉ ለአስቴር አስታወቃት፡፡ 10እር
ሷም ለመርዶክዮስ እንዲህ እንዲለው ነገረ
ችው፤ 11 "የንጉሡ ባሮችና በንጉሡ አውራ
ጃዎች የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ወንድም ሆነ
ሴት፣ ማንም ሰው ሳይጠራ ንጉሡ ወዳለ
በት ወደ ውስጠኛው አደባባይ የሚገባ፣
ንጉሡ አንድ ሕግ ብቻ እንዳለው ያውቃል፤
ይኸውም እንዲህ ያደረገው ሰው ይገደላል፤
አንድ ሰው ከእንዲህ ዐይነቱ ሞት የሚ
ተርፈው፣ ንጉሡ የወርቅ ዘንጉን ሲዘረጋ
ለት ብቻ ነው፡፡ እኔ ግን ወደ ንጉሡ ዘንድ
እንድገባ ከተጠራሁ ከሠላሳ ቀን በላይ
ሆነ፡፡"
12የአስቴር ቃል ለመርዶክዮስ በተነገረው
ጊዜ፣ 13ይህን መልስ ላከባት፤ "አንቺ በን
ጉሥ ቤት በመሆንሽ ብቻ ሌላው የአይሁድ
ሕዝብ ሲጠፋ አንቺ የምትተርፊ እንዳይ
መስልሽ፤ 14በዚህ ጊዜ አንቺ ዝም ብትዪ፣
ለአይሁድ ርዳታና ትድግና ከሌላ ስፍራ
ይመጣላቸዋል፤ አንቺና የአባትሽ ቤት
ግን ትጠፋላችሁ፤ ደግሞስ አንቺ ንግሥት
ለመሆን የበቃሽው ለዚህ ጊዜ እንደ ሆነ
ማን ያውቃል?"
15ከዚያም አስቴር ለመርዶክዮስ ይህን
መልስ ላከችበት፤ 16"ሂድና በሱሳ ያሉትን
አይሁድ ሁሉ በአንድነት ሰብስብ፤ ስለ
እኔም ጹሙልኝ፤ ቀንም ይሁን ሌሊት
ለሦስት ቀን አትብሉ፤ አትጠጡም፡፡ እኔና
ደንገጡሮቼም እናንተ እንደምታደርጉት
ሁሉ እንጾማለን፤ ይህ ከተፈጸመ በኋላ ግን
ነገሩ ምንም እንኳ ከሕግ ውጭ ቢሆንም፣
ወደ ንጉሡ ዘንድ እሄዳለሁ፤ ከጠፋሁም
ልጥፋ፡፡"

4፥7 አስ7፥4
4፥11 አስ2፥14፤
5፥2፤8፥4፤መዝ125፥3፤
ዳን2፥9
4፥14 ዘፍ45፥7፤
50፥20፤ዘዳ28፥29፤
አስ9፥16፡22፤ኢዮ
34፥29፤መዝ28፥1፤
35፥22፤መክ3፥7፤
ኢሳ 42፥14፤57፥11፤
62፥1፤ 64፥12፤
አሞ5፥13
4፥16 ዘፍ43፥14፤
2ዜና20፥3፤አስ9፥31

5፥1 ምሳ21፥1፤
ሕዝ 16፥13
5፥2 አስ4፥11
5፥3 አስ7፥2፤
ዳን5፥16፤ማር6፥23
5፥6 አስ1፥10፤
9፥12፤ዳን5፥16፤
ማር 6፥23
5፥8 አስ2፥15፤
1ነገ3፥15
5፥9 አስ2፥21፤
3፥3፤ ምሳ14፥17
5፥10 አስ6፥13
5፥11 አስ9፥10፡13፤
ምሳ13፥16
5፥12 ኢዮ22፥29፤
ምሳ16፥18፤29፥23

17ስለዚህ መርዶክዮስ ሄደ፤ የአስቴርንም
ትእዛዝ ሁሉ ፈጸመ፡፡

## አስቴር ለንጉሡ ያቀረበችው ልመና

5 በሦስተኛው ቀን አስቴር የክብር ልብ
ሷን ለብሳ በንጉሡ አዳራሽ ፊት
ለፊት ባለው በቤተ መንግሥቱ ውስጠኛ
አደባባይ ገብታ ቆመች፡፡ ንጉሡም አዳራሹ
ውስጥ በመግቢያው ትይዩ በዙፋኑ ላይ
ተቀምጦ ነበር፡፡ 2ንግሥት አስቴር በአደባ
ባዩ ላይ ቆማ ሲያያት ደስ አለው፤ በእጁ
የያዘውን የወርቅ ዘንግ ዘረጋላት፤ አስቴ
ርም ቀረብ ብላ የዘንጉን ጫፍ ነካች፡፡
3ከዚያም ንጉሡ፣ "ንግሥት አስቴር ሆይ፤
ለምን መጣሽ? ከእኔ የምትፈልጊውስ
ምንድን ነው? እስከ መንግሥቴ እኩሌታ
እንኳ ቢሆን ይሰጥሻል" አላት፡፡
4አስቴርም መልሳ፣ "ንጉሡን ደስ የሚ
ያሰኘው ቢሆን፣ ባዘጋጀሁለት ግብዣ ላይ
ንጉሡ ዛሬ ከሐማ ጋር ይገኝልኝ" አለች፡፡
5ንጉሡም፣ "አስቴር ያለችውን እንድን
ፈጽም፣ ሐማን በፍጥነት ጥሩት" አለ፡፡
ስለዚህ ንጉሡና ሐማ አስቴር ወዳዘጋጀችው
ግብዣ ሄዱ፡፡ 6የወይን ጠጅ እየጠጡ ሳለ
ንጉሡ ዳግመኛ አስቴርን፣ "እስቲ የምት
ፈልጊው ምንድን ነው? ይሰጥሻል፤ ደግ
ሞስ የምትጠዪቂው ምንድን ነው? እስከ
መንግሥቴ እኩሌታ እንኳ ቢሆን ይፈቀድ
ልሻል" አላት፡፡
7አስቴርም እንዲህ ስትል መለሰች፤
"ልመናዬም፣ ጥያቄዬም ይህ ነው፤ 8በንጉሡ
ዘንድ ሞገስ ካገኘሁና የምፈልገውን ሊሰጠ
ኝና ልመናዬንም ሊፈጽምልኝ ንጉሡን
ደስ ካሰኘው፣ ንጉሡና ሐማ በማዘጋጅላቸው
ግብዣ ላይ ነገ ይገኙልኝ፡፡ ከዚያም እኔ
ለንጉሡ ጥያቄ መልስ እሰጣለሁ፡፡"

## ሐማ በመርዶክዮስ ላይ ያወረደው ቍጣ

9ሐማ በዚያን ቀን ደስ ብሎትና መን
ፈሱ ረክቶ ወጣ፤ ነገር ግን መርዶክዮስን
በንጉሡ በር ላይ ሲያየው ከተቀመጠበት
አለመነሣቱንና በፊቱም አለመንቀጥቀጡን
ሲመለከት፣ ቍጣው በመርዶክዮስ ላይ
ነደደ፡፡ 10ሐማ ግን እንደ ምንም ራሱን ተቈ
ጣጥሮ ወደ ቤቱ ሄደ፡፡
ወዳጆቹንና ሚስቱን ዞሳራን አስጠርቶ
በአንድነት ከሰበሰባቸው በኋላ፣ 11ሐማ ስለ
ሀብቱ ታላቅነት፣ ስለ ልጆቹ ብዛት እንዲ
ሁም ንጉሡ የቱን ያህል እንዳከበረው፣
ከሌሎቹም መኳንንትና ሹማምት ይበልጥ
እንዴት ከፍ ከፍ እንዳደረገው እያጋነነ
ነገራቸው፡፡ 12ሐማም፣ "ምን ይኸ ብቻ"
አለ፤ "ንግሥት አስቴር ባዘጋጀችው ግብዣ

ላይ ከንጉሡ ጋር እንድገኝ የጋበዘችው
ሰው አንድ እኔ ብቻ ነኝ፤ ነገም ከንጉሡ
ጋር ጋብዛኛለች። 13ነገር ግን አይሁዳዊው
መርዶክዮስ በንጉሡ በር ላይ ተቀምጦ
ካየሁት ይህ ሁሉ እኔን ደስ አያሰኘኝም።”
14ሚስቱ ዞሳራና ወዳጆቹ በሙሉ፣ “ቁመቱ
አምሳ ክንድ[ለ] የሆነ መስቀያ አስተክልና
መርዶክዮስ እንዲሰቀልበት በጠዋት ለንጉሡ
ንገረው፤ ከዚያም ደስ ብሎህ ከንጉሡ ጋር
ወደ ግብዣው ግባ” አሉት። ይህም ሐሳብ
ሐማን እጅግ ደስ አሰኘው፤ መስቀያውንም
አስተከለ።

## መርዶክዮስ ከፍ ከፍ አለ

6 በዚያች ሌሊት ንጉሡ እንቅልፍ መተ
ኛት አልቻለም። ስለዚህ በዘመነ መን
ግሥቱ የተመዘገበው የታሪክ መጽሐፍ
ቀርቦ እንዲነበብለት አዘዘ። 2በዚያም በሩን
ከሚጠብቁት ከንጉሡ የጦር አዛዦች ሁለቱ፣
ገበታና ታራ ንጉሥ ጠረክሲስን ለመግደል
አሢረው እንደ ነበርና ይህንንም መርዶክ
ዮስ እንደ ተናገረ ተጽፎ ተገኘ።
3ንጉሡም፣ “ታዲያ ይህን በማድረጉ
መርዶክዮስ ያገኘው ክብርና ማዕረግ ምን
ድን ነው?” ሲል ጠየቀ።
የቅርብ አገልጋዮቹም፣ “ምንም አልተደ
ረገለትም” ብለው መለሱ።
4ንጉሡም፣ “በአደባባዩ ማን አለ?” ሲል
ጠየቀ። በዚህ ጊዜ ሐማ በተከለው ዕን
ጨት ላይ መርዶክዮስ ይሰቀል ዘንድ ለን
ጉሡ ለመናገር በውጭ በኩል ወደሚገኘው
የቤተ መንግሥቱ አደባባይ ገና መድረሱ
ነበር።
5የቅርብ አገልጋዮቹም፣ “እነሆ፤ ሐማ
በአደባባዩ ቆሞአል” አሉት።
ንጉሡም፣ “ግባ በሉት” ብሎ አዘዘ።
6ሐማ በገባ ጊዜ ንጉሡ፣ “ንጉሥ ሊያ
ከብረው ለወደደው ሰው ምን ሊደረግለት
ይገባል?” ሲል ጠየቀው።
በዚህ ጊዜ ሐማ፣ “ንጉሡ ከእኔ ይልቅ
የሚያከብረው ማን አለ?” ሲል በልቡ ዐሰበ።
7ስለዚህ ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ንጉሡ
ሊያከብረው ለወደደው ሰው፣ 8ንጉሡ
የሚጐናጸፈው ልብሰ መንግሥት፣ ንጉሡም
የሚቀመጥበትና የንጉሡን ዘውድ በራሱ ላይ
ያደረገ ፈረስ ይምጣለት። 9ከዚያም ልብ
ሱና ፈረሱ እጅግ ከከበሩት ከንጉሡ ልዑላን
መሳፍንት በአንዱ እጅ ይሰጥለት። ንጉሡ
ሊያከብረው የወደደውን ሰው ያልብሱት፤
በፈረሱም ላይ አስቀመጠውም በከተማ
ዪቱ ዋና ዋና መንገዶች ላይ እየመሩ፣
‘ንጉሡ ሊያከብረው ለሚወደው ሰው ይህ
ተደርጎለታል’ ይበሉ።”
10ንጉሡም ሐማን፣ “በል ፈጥነህ ሂድ፤
ልብሱንና ፈረሱን ውሰድ፤ በንጉሡ በር
ላይ ለሚቀመጠው ለአይሁዳዊው ለመር
ዶክዮስም ልክ እንዳልኸው አድርግለት፤ ከተ
ናገርኸውም አንዳች ነገር እንዳይጐድል”
ሲል አዘዘው።
11ስለዚህ ሐማ ልብሱንና ፈረሱን ወስዶ
መርዶክዮስን አለበሰው፤ በዋና ዋና መንገ
ዶች ላይ እየመራም፣ “ንጉሥ ሊያከብረው
ለሚወደው ሰው ይህ ተደርጎለታል” እያለ
በፊቱ ያውጅ ነበር።
12ከዚያም በኋላ መርዶክዮስ ወደ ንጉሡ
በር ተመለሰ፤ ሐማ ግን አዝኖና ራሱን
ተከናንቦ በጥድፊያ ወደ ቤቱ ሄደ። 13የደ
ረሰበትንም ሁሉ ለሚስቱ ለዞሳራና ለወዳ
ጆቹ ሁሉ ነገራቸው።
አማካሪዎቹና ሚስቱ ዞሳራም፣ “በፊቱ
መውደቅ የጀመርህለት መርዶክዮስ ዘሩ
ከአይሁድ ወገን ከሆነ፣ ልትቋቋመው አት
ችልም፤ ያለ ጥርጥር ትጠፋለህ” አሉት።
14ከእርሱ ጋር በመነጋገር ላይ ሳሉ፣ የንጉሡ
ጃንደረቦች ደርሰው ሐማን አስቴር ወዳዘጋጀ
ችው ግብዣ አጣደፉት።

## ሐማ ተሰቀለ

7 ስለዚህ ንጉሡና ሐማ ከንግሥት አስ
ቴር ጋር ለመጋበዝ ሄዱ፤ 2በሁለተ
ኛውም ቀን የወይን ጠጅ እየጠጡ ሳለ፣
ንጉሡ እንደ ገና፣ “ንግሥት አስቴር ሆይ፤
የምትለምኚው ምንድን ነው? ይሰጥሻል፤
የምትጠይቂውስ ምንድን ነው? እስከ መን
ግሥቴ እኩሌታ እንኳ ቢሆን ይደረግል
ሻል” አላት።
3ከዚያም ንግሥት አስቴር እንዲህ ስትል
መለሰች፤ “ንጉሥ ሆይ፤ በፊትህ ሞገስ አግ
ኝቼና ግርማዊነትህን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ፣
ሕይወቴን ታደጋት፤ ልመናዬ ይህ ነው፤
ሕዝቤን አትርፍ፤ ጥያቄዬም ይኸው ነው።
4እኔና ሕዝቤ ለጥፋት፣ ለዕርድና ለመደ
ምሰስ ተሸጠናልና። ወንዶችና ሴቶች ባሮች
ለመሆን የተሸጥን ቢሆን ኖሮ፣ ዝም ባልሁ
ነበር፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ጭንቀት
ንጉሡን ለማስቸገር የሚበቃ አይደለም[ሐ]።”
5ንጉሥ ጠረክሲስም ንግሥት አስቴርን፣
“ለመሆኑ እርሱ ማን ነው? እንዲህ ያለ
ውን ነገር ለማድረግ እስከዚህ የደፈረውስ
ሰው የታለ?” ሲል ጠየቀ።
6አስቴርም፣ “ያ ባላጋራና ጠላት ይህ
ክፉው ሐማ ነው” አለች።

[ለ]14 23 ሜትር ያህል ነው።
[ሐ]4 ወይም፣ *ዝም ባልሁም ነበር፤ ነገር ግን ባለጋራችን የሚሰ ጠው ካሣ ንጉሡ ከሚያጣው ነገር ጋር ከቶ አይነጻጸርም*

5፥13 አስ2፥19
5፥14 ዕዝ6፥11፤ አስ7፥9
6፥1 አስ2፥23፤ ዳን2፥1፤6፥18
6፥2 አስ2፥21-23
6፥3 መክ9፥13-16
6፥8 ዘፍ41፥42፤ 1ነገ1፥33፤ኢሳ52፥1
6፥9 ዘፍ41፥43
6፥11 ዘፍ41፥42
6፥12 2ሳሙ15፥30፤ አስ7፥8፤ኤር14፥3፡4፤ ሚክ3፥7
6፥13 አስ5፥10፤ 7፥7፤መዝ57፥6፤ ምሳ 26፥27፤28፥18
6፥14 1ነገ3፥15
7፥1 ዘፍ40፥20-22፤ ማቴ22፥1-14
7፥2 አስ፥10፤5፥3፤ 9፥12
7፥3 አስ2፥15
7፥4 አስ3፥9፤4፥7

ከዚያም ሐማ በንጉሡና በንግሥቲቱ
ፊት እጅግ ደነገጠ። 7ንጉሡ ከተቀመጠ
በት በቍጣ ተነሣ፤ የወይን ጠጁንም ትቶ
ወደ ቤተ መንግሥቱ የአትክልት ቦታ
ሄደ። ሐማ ግን ንጉሡ ሊያጠፋው ቈርጦ
መነሣቱን ስላወቀ፣ ንግሥት አስቴር ሕይ
ወቱን እንድታተርፍለት ለመማጠን በዚ
ያው ቀረ።
8ንጉሡ ከቤተ መንግሥቱ የአትክልት
ቦታ ወደ ግብዣው አዳራሽ ሲመለስ አስ
ቴር ደገፍ ባለችበት ድንክ ዐልጋ ላይ ሐማ
ተደፍቶ ነበር።
ንጉሡም፣ "ይባስ ብሎ አብራኝ ያለች
ውን ንግሥት በገዛ ቤቴ ሊደፍራት ያስባ
ልን?" ሲል ተናገረ።
ይህ ቃል ከንጉሡ አፍ ገና እንደ ወጣ፣
የሐማን ፊት ሸፈኑት። 9ከዚያም ንጉሡን
በቅርብ ከሚያገለግሉት ጃንደረቦች አንዱ
የሆነው ሐርቦና፣ "እነሆ ቁመቱ አምሳ
ክንድ[መ] የሆነ ግንድ በሐማ ቤት አጠገብ
ተተክሎአል፤ ይህን ያዘጋጀው ንጉሡን ለማ
ዳን በጎ ነገር ለተናገረው ለመርዶክዮስ
ነው" አለ።
ንጉሡም፣ "በዚሁ ላይ ስቀሉት" አለ።
10ስለዚህ ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው ግንድ
ላይ ሐማን ሰቀሉት፤ ከዚያም የንጉሡ ቍጣ
በረደ።

## ንጉሡ በአይሁድ ስም የተናገረው ዐዋጅ

8 በዚያኑ ዕለት ንጉሥ ጠረክሲስ የአይ
ሁድን ጠላት የሐማን ቤት ንብረት
ለንግሥት አስቴር ሰጣት፤ አስቴርም መር
ዶክዮስ እንዴት እንደሚዛመዳት ለንጉሡ
ነግራው ስለ ነበር፣ መርዶክዮስ ወደ ንጉሡ
ዘንድ ቀረበ። 2ንጉሡ ከሐማ መልሶ የወ
ሰደውን ባለ ማኅተም ቀለበት አውልቆ
ለመርዶክዮስ ሰጠው፤ አስቴርም መርዶክ
ዮስን በሐማ ቤት ንብረት ላይ ሾመ
ችው።
3አስቴር በንጉሡ እግር ላይ ወድቃ በማ
ልቀስ ልመናዋን እንደ ገና አቀረበች።
አጋጋዊው ሐማ በአይሁድ ላይ የሸረበው
ክፉ ሤራ እንዲሽር ለመነችው። 4ከዚያም
ንጉሡ የወርቅ ዘንጉን ለአስቴር ዘረጋላት፤
እርሷም ተነሥታ በፊቱ ቆመች።
5እንዲህም አለች፤ "ንጉሡን ደስ የሚያ
ሰኘውና እኔም በፊቱ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፣
ጉዳዩም በንጉሡ ዘንድ ተገቢ ሆኖ ከተገ
ኘና በእኔም ደስ ከተሰኘ፣ የአጋጋዊው የሐ
መዳቱ ልጅ ሐማ በንጉሡ አውራጃዎች
ሁሉ የሚገኙትን አይሁድ ለማጥፋት የሸረ
በውን ሤራና የጻፈውን ደብዳቤ የሚሽር
ትእዛዝ ይጻፍ። 6በሕዝቤ ላይ መዐት ሲወ
ርድ እያየሁ እንዴት ልታገሥ እችላለሁ?
የቤተ ሰቤንስ መጥፋት እያየሁ እንዴት
መቋቋም እችላለሁ?"
7ንጉሥ ጠረክሲስም ለንግሥት አስቴ
ርና ለአይሁዳዊው ለመርዶክዮስ እንዲህ
ሲል መለሰላቸው፤ "እነሆ ሐማ አይሁድን
ለማጥፋት ስላቀደ፣ ቤት ንብረቱን ለአስ
ቴር ሰጥቻለሁ፤ እርሱንም በዕንጨት ላይ
ሰቅለውታል። 8በንጉሥ ስም የተጻፈና በቀ
ለበቱ የታተመ ደብዳቤ ሊሻር ስለማይ
ችል፣ እናንተ ደግሞ አይሁድን በተመለ
ከተ መልካም መስሎ የታያችሁን ሌላ ዐዋጅ
በንጉሡ ስም ጽፋችሁ በንጉሡ የቀለበት
ማኅተም አትሙት።"
9ኒሳን በተባለው በሦስተኛው ወር ሃያ
ሦስተኛ ቀን የቤተ መንግሥቱ ጸሓፊዎች
በአስቸኳይ ተጠርተው ነበር፤ እነርሱም
የመርዶክዮስን ትእዛዝ ሁሉ ለአይሁድ፣
እንዲሁም ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮ
ጵያ ድረስ፣ በአንድ መቶ ሃያ ሰባት
አውራጃዎች ለሚገኙ እንደራሴዎች፣ የአው
ራጃ ገዦችና መኳንንት ሁሉ ጻፉ። እነዚ
ህም ትእዛዞች የተጻፉት በእያንዳንዱ አው
ራጃ ፊደልና በእያንዳንዱ ሕዝብ ቋንቋ፣
እንደዚሁም ለአይሁድ በገዛ ፊደላቸውና
በገዛ ቋንቋቸው ነበር። 10መርዶክዮስ ትእ
ዛዙን በንጉሥ ጠረክሲስ ስም ጽፎ በንጉሡ
የቀለበት ማኅተም አተመው፤ ከዚያም በተ
ለይ ለንጉሡ በተገሩ ፈጣን ፈረሶች በሚጋ
ልቡ መልእክተኞች እጅ ላከው።
11የንጉሡም ዐዋጅ በየከተማው የሚኖሩ
አይሁድ ሁሉ እንዲሰበሰቡና ራሳቸውን
ከጥቃት እንዲከላከሉ እንዲሁም በራሳቸው፣
በሚስቶቻቸውና በልጆቻቸው ላይ አደጋ የሚ
ያደርስባቸውን የየትኛውንም ዜጋ ወይም
አውራጃ የታጠቀ ኀይል እንዲያጠፉ፣ እን
ዲገድሉ፣ እንዲደመስሱና የጠላቶቻቸውን
ሀብት እንዲዘርፉ ፈቀደላቸው። 12አይሁድ
በመላው የንጉሥ ጠረክሲስ አውራጃ ሁሉ
ይህን እንዲፈጽሙ የተወሰነው አዳር በተባ
ለው በዐሥራ ሁለተኛው ወር ዐሥራ ሦስ
ተኛ ቀን ነበር። 13አይሁድ በዚያን ቀን ጠላ
ቶቻቸውን ለመበቀል ዝግጁ እንዲሆኑ፣
የዋናው ዐዋጅ ቅጅ ሕግ ወደየአውራጃው
እንዲላክና የየአገሩም ሕዝብ እንዲያውቀው
ተደረገ።
14በቤተ መንግሥቱ ፈረሶች የተቀመጡ
መልእክተኞችም፣ በንጉሡ አስቸኳይ ትእ
ዛዝ ጋልበው ወጡ፤ ዐዋጁም በሱሳ ግንብ
ተነገረ።
15መርዶክዮስ ሰማያዊና ነጭ የቤተ

7፥7 ዘፍ34፥7፤ 2ነገ21፥18፤አስ1፥12፤ 6፥13፤ምሳ19፥12፤ 20፥1-2
7፥8 ዘፍ34፥7፤ 39፥14፤አስ1፥6፤6፥12፤ ዮሐ13፥23
7፥9 ዘዳ21፥22-23፤ አስ1፥10፤5፥14፤ መዝ7፥14፡16፤9፥16፤ ምሳ11፥5-6፤ማቴ7፥2
7፥10 ዘፍ40፥22፤ አስ2፥1፤9፥25፤ ምሳ10፥28፤ዳን6፥24
8፥1 ምሳ22፥22-23
8፥2 ዘፍ24፥22፤ 41፥41፡42፤ ምሳ13፥22፤ 14፥35፤ዳን2፥48
8፥3 ዘፀ17፥8-16
8፥4 አስ4፥11
8፥5 አስ2፥15
8፥6 ዘፍ44፥34
8፥7 ዘዳ21፥22-23
8፥8 ዘፍ38፥18፤ 41፥42፤አስ1፥19፤ 3፥12-14፤ዳን6፥15
8፥9 ነህ13፥24፤ አስ1፥1
8፥11 ዘፍ14፥23፤ አስ3፥13፤9፥15፡16
8፥12 አስ3፥13፤ 9፥1
8፥13 አስ3፥14
8፥14 አስ3፥15
8፥15 ዘፍ41፥42፤ አስ3፥15፤9፥4፤10፥2፤ 2ሳሙ12፥30

[መ]9 23 ሜትር ያህል ነው።

መንግሥት ልብስ ለብሶ፣ ትልቅ የወርቅ
አክሊል ደፍቶ፣ ከቀጭን በፍታና ከሐምራዊ
ግምጃ የተሠራ መጐናጸፊያ ተጐናጽፎ
ከንጉሡ ፊት ወጣ፤ የሱሳ ከተማም ደስታ
የተሞላበት በዓል አከበረች። 16ጊዜውም
ለአይሁድ የደስታና የፈንጠዝያ፣ የተድላና
የክብር ወቅት ሆነላቸው። 17የንጉሡ ዐዋጅ
በደረሰበት በእያንዳንዱ አውራጃና በእያን
ዳንዱ ከተማ አይሁድ ደስ አላቸው፤ ሐሤት
አደረጉ፤ የፈንጠዝያና የደስታም ቀን ሆነ
ላቸው። አይሁድን ከመፍራታቸው የተነሣ፣
ከሌሎች አገር ዜጎች ብዙ ሕዝብ አይሁድ
ሆኑ።

## የአይሁድ ድል ማድረግ

9 አዳር በተባለው በዐሥራ ሁለተኛው
ወር ዐሥራ ሦስተኛ ቀን፣ በንጉሡ ትእ
ዛዝ የወጣው ዐዋጅ የሚፈጸምበት ዕለት
ነበር። በዚህም ዕለት የአይሁድ ጠላቶች
የበላይነቱን እንደሚያገኙ ተማምነው ነበር፤
ሁኔታው ግን ተለወጠና አይሁድ በሚጠሏ
ቸው ላይ የበላይነትን አገኙ። 2የእነርሱን
መጥፋት በሚፈልጉ ወገኖች ላይ አደጋ
ለመጣል አይሁድ በንጉሥ ጠረክሲስ አው
ራጃዎች ሁሉ ባሉት ከተሞቻቸው ተሰበ
ሰቡ። የሌሎቹ አገር ዜጎች ሕዝብ ሁሉ ፈር
ተዋቸው ስለ ነበር፣ ማንም ሊደፍራቸው
አልቻለም። 3የየአውራጃው መኳንንት ሁሉ፣
እንደራሴዎች፣ የአውራጃ ገዦች እንዲ
ሁም የንጉሡ አስተዳዳሪዎች አይሁድን
ረዷቸው፤ ይህን ያደረጉትም መርዶክዮስን
ስለ ፈሩ ነበር። 4መርዶክዮስ በቤተ መንግ
ሥቱ ታዋቂ ሆነ፤ ዝናው በየአውራጃው
ሁሉ ተሰማ፤ ኀይሉም እየበረታ ሄደ።
5ስለዚህ አይሁድ ጠላቶቻቸውን ሁሉ
በሰይፍ እየመቱ ገደሏቸው፤ አጠፏቸውም፤
በሚጠሏቸውም ላይ ደስ ያላቸውን አደ
ረጉ። 6አይሁድ በሱሳ ግንብ አምስት መቶ
ሰው ገደሉ፤ አጠፉም። 7ፓርሻንዳታን፣
ደልፎንን፣ አስፓታን፣ 8ፖራታን፣ አዳል
ያን፣ አሪዳታን፣ 9ፓርማሽታን፣ አሪሳይን፣
አሪዳይንና ዋይዛታንም ገደሉ፤ 10እነዚህም
የአይሁድ ጠላት የሆነው የሐመዳቱ ልጅ
የሐማ ዐሥር ወንዶች ልጆች ነበሩ። በም
ርኮው ላይ ግን እጃቸውን አልዘረጉም።
11በሱሳ ግንብ የተገደሉት ሰዎች ብዛት
በዚያኑ ዕለት ለንጉሡ ተነገረው። 12ንጉሡም
ንግሥት አስቴርን፣ "አይሁድ በሱሳ ግንብ
አምስት መቶ ሰውና ዐሥሩን የሐማ
ልጆች ገድለዋል፤ አጥፍተዋልም። በተቀሩት
በንጉሡ አውራጃዎችስ ምን አድርገው ይሆን?
አሁንስ የምትለምኚው ምንድን ነው? ይሰ
ጥሻል፤ የምትጠይቂውስ ምንድን ነው?

8፥16 አስ4፥1-3፤
መዝ97፥10-12፤
112፥4፤ኤር29፥4-7
8፥17 ዘፀ15፥14፡
16፤ዘዳ11፥15፤አስ
9፥3፤መዝ35፥27፤
45፥15፤51፥8፤
ምሳ11፥10፤ዳን6፥26
9፥1 አስ3፥12-14፤
8፥12፤ምሳ22፥22-23፤
ኤር29፥4-7
9፥2 ዘፍ22፥17፤
መዝ35፥26፤40፥14፤
70፥2፤71፥13፡24
9፥3 ዕዝ8፥36፤አስ
8፥17
9፥4 ዘፀ11፥3፤
2ሳሙ3፥1፤
1ዜና11፥9፤አስ8፥15
9፥5 ዘዳ25፥17-19፤
1ሳሙ15፥3፤ዕዝ4፥6
9፥10 ዘፍ14፥23፤
1ሳሙ14፥32፤15፥33፤
አስ3፥13፤5፥11፤
መዝ127፥3-5
9፥12 አስ5፥6፤
7፥2
9፥13 ዘዳ21፥22-23፤
አስ5፥11
9፥14 ዕዝ6፥14
9፥15 ዘፍ14፥23፤
አስ8፥11
9፥16 ዘዳ25፥19፤
1ዜና4፥43፤
አስ4፥14፤8፥11
9፥17 1ነገ3፥15
9፥19 አስ2፥9፤3፥7፤
ራእ11፥10
9፥22 2ነገ25፥30፤
ነህ8፥10፡12፤አስ4፥14፤
መዝ30፥11-12
9፥24 ዘፀ17፥8-16፤
ዘሌ16፥8፤አስ3፥6፡7

ይፈቀድልሻል" አላት።
13አስቴርም፣ "ንጉሥን ደስ የሚያሰኘው
ከሆነ፣ በሱሳ የሚኖሩ አይሁድ የዛሬውን
ዐዋጅ ነገም እንዲደግሙት ፈቃድህ ይሁን፤
ዐሥሩ የሐማ ወንዶች ልጆችም ዕንጨት
ላይ ይሰቀሉ" አለች።
14ንጉሡም ይህ እንዲሆን አዘዘ። በሱሳ
ዐዋጅ ተነገረ፤ ዐሥሩንም የሐማ ወንዶች
ልጆች ሰቀሏቸው። 15በሱሳ የሚኖሩ አይሁድ
አዳር በተባለው ወር በዐሥራ አራተኛው
ቀን በአንድነት መጡ፤ በሱሳም ሦስት መቶ
ሰዎች ገደሉ፤ በምርኮው ላይ ግን እጃቸ
ውን አልዘረጉም።
16በዚህ ጊዜ በሌሎች በንጉሡ አውራጃ
ዎች የሚኖሩ የተቀሩት አይሁድ ራሳቸ
ውን ለመከላከልና ከጠላቶቻቸውም ለመ
ገላገል ተሰበሰቡ፤ ከሚጠሏቸውም ሰባ አም
ስት ሺህ ገደሉ፤ በምርኮው ላይ ግን እጃ
ቸውን አልዘረጉም። 17ይህ የሆነው አዳር
በተባለው ወር ዐሥራ ሦስተኛ ቀን ነበር፤
በዐሥራ አራተኛው ቀን ዐረፉ፤ ዕለቱንም
የተድላና የደስታ ቀን አድርገው ዋሉ።

## የፉሪም በዓል መከበር

18በሱሳ የሚኖሩ አይሁድ ግን በዐሥራ
ሦስተኛውና በዐሥራ አራተኛው ቀን ተሰ
ብስበው ነበር፤ ከዚያም በዐሥራ አምስተኛው
ቀን ዐረፉ፤ ዕለቱንም የተድላና የደስታ
ቀን አድርገው ዋሉ።
19በየመንደሩ የሚኖሩ የገጠር አይሁድ፣
የአዳርን ወር ዐሥራ አራተኛ ቀን የተድላና
የደስታ፣ እርስ በርሳቸውም ስጦታ የሚለ
ዋወጡበት ቀን አድርገው የሚያከብሩት
ከዚሁ የተነሣ ነው።
20መርዶክዮስ የተፈጸሙትን እነዚህን
ድርጊቶች ጻፈ፤ ደብዳቤ አዘጋጅቶም በመ
ላው የንጉሥ ጠረክሲስ አውራጃ በቅር
ብና በሩቅ ለሚገኙት አይሁድ ሁሉ ላከ፤
21የላከውም የአዳርን ወር ዐሥራ አራተ
ኛና ዐሥራ አምስተኛ ቀን በየዐመቱ እንዲ
ያከብሩ ነው፤ 22የሚያከብሩበትም ምክን
ያት አይሁድ ከጠላቶቻቸው ዕረፍት ያገ
ኙበት፣ ሐዘናቸው ወደ ደስታ፣ ልቅሷቸውም
ወደ ክብረ በዓል የተለወጠበት ቀን ስለ
ሆነ ነው። ቀኖቹንም የተድላና የደስታ
ቀኖች አድርገው፣ እርስ በርሳቸውም የም
ግብ ስጦታ እየተለዋወጡና ለድኾችም
ስጦታ እየሰጡ እንዲያከብሩ ጻፈላቸው።
23ስለዚህ አይሁድ መርዶክዮስ የጻፈላቸ
ውን ለመፈጸምና የጀመሩትን በዓል ለማ
ክበር ተስማሙ፤ 24ምክንያቱም የአይሁድ
ሁሉ ጠላት የሆነው የአጋጋዊው የሐ
መዳቱ ልጅ ሐማ አይሁድን ለማጥፋት

አሚሮ ነበር፤ ሊፈጃቸውና ሊያጠፋቸውም
ፉር የተባለ ዕጣ ጥሎ ነበር። 25ሜራው
በንጉሡ ዘንድ እንደ ታወቀ[ሥ] ሐማ በአ
ይሁድ ላይ የሸረበው ሤራ በገዛ ራሱ ላይ
እንዲጠመጠም፣ እርሱና ወንዶች ልጆቹም
በዕንጨት ላይ እንዲሰቀሉ የጽሑፍ ትእዛዝ
አስተላለፈ። 26ስለዚህ እነዚህ ቀኖች ፉር
ከሚለው ቃል “ፉሪም” ለመባል በቁ።
በዚህ ደብዳቤ ስለ ተጻፈው ሁሉ፣ ስላዩ
ትና ስለ ደረሰባቸውም ነገር ሁሉ፣ 27አይ
ሁድ በታዘዘውና በተወሰነው ጊዜ እነርሱና
ዘሮቻቸው፣ እነርሱን የተጠጓቸውም ሁሉ
እነዚህን ሁለት ቀኖች በየዓመቱ ባለማቋ
ረጥ እንዲያከብሩ ሥርዐት አድርገው ራሳ
ቸው ወሰኑ። 28እነዚህም ቀኖች በእያንዳንዱ
ትውልድ፣ በእያንዳንዱ ቤተ ሰብ፣ በእያን
ዳንዱ አውራጃና በእያንዳንዱ ከተማ መታ
ሰብና መከበር ይኖርባቸዋል፤ ይኸውም
እነዚህ የፉሪም ቀኖች በአይሁድ ዘንድ ሳይ
ከበሩ እንዳይቀሩ፤ መታሰቢያቸውም ከዘሮ
ቻቸው መካከል እንዳይደመሰስ ነው።
29ስለዚህ የአቢካኢል ልጅ ንግሥት አስ
ቴር ከአይሁዳዊው ከመርዶክዮስ ጋር በመ
ሆን፣ ፉሪምን አስመልክተው ይህችን ሁለ
ተኛዪቱን ደብዳቤ ለማጽናት በሙሉ ሥል
ጣን ጻፉ። 30መርዶክዮስም የመልካም
ምኞት መግለጫና ማረጋገጫ የሆነውን

9፥25 ዘዳ21፥22-23፤ አስ7፥10፤መዝ7፥16
9፥26 አስ3፥7
9፥29 አስ2፥15
9፥30 አስ1፥1
9፥31 አስ4፥1-3፡16
10፥1 መዝ72፥10፤ 97፥1
10፥2 ዘፍ41፥44፤ አስ2፥23፤8፥15
10፥3 ዘፍ41፥40፡ 43፤ነህ2፥10፤ ኤር29፥4-7፤ ዳን5፥7፤6፥3

ደብዳቤ በጠረክሲስ ግዛት ውስጥ በሚገ
ኙት አንድ መቶ ሃያ ሰባት አውራጃዎች
ለሚኖሩት አይሁድ ሁሉ ላከ፤ 31የላከውም
አይሁዳዊው መርዶክዮስና ንግሥት አስቴር
ባወጁላቸውና እንደዚሁም የጾሙንና የሰ
ቈቃውን ጊዜ በሚመለከት ለራሳቸውና
ለዘራቸው ባጸኑት ውሳኔ መሠረት እነዚህ
የፉሪም ቀኖች በተወሰነላቸው ጊዜ እንዲ
ከበሩ ነው። 32የአስቴር ዐዋጅ ስለ ፉሪም
የወጣውን ሥርዐት አጸና፤ ይህም በመዝገብ
ተጻፈ።

## የመርዶክዮስ ታላቅነት

10 ንጉሥ ጠረክሲስ እስከ ባሕር ዳርቻ
በሚዘልቀው ግዛቱ ሁሉ ላይ ግብር
ጣለ። 2የኀይሉና የብርታቱ ሥራ ሁሉ እን
ዲሁም ንጉሡ መርዶክዮስን ለዚህ የላቀ
ማዕረግ እንዴት እንዳደረሰው የሚናገረው
በሜዶንና በፋርስ የታሪክ መጽሐፍ የተጻፈ
አይደለምን? 3አይሁዳዊው መርዶክዮስ
በማዕረግ ከንጉሡ ከጠረክሲስ ቀጥሎ ሁለ
ተኛ፣ ከአይሁድ መካከልም ቀዳሚውን ስፍራ
የያዘ ሰው ነበር፤ ለወገኖቹ መልካም በማ
ድረጉና ለአይሁድም ሁሉ ደኅንነት የቆመ
በመሆኑ፣ በብዙዎቹ አይሁድ ወገኖቹ ዘንድ
እጅግ የተከበረ ነበር።

[ሥ]25 ወይም፣ *አስቴር በንጉሡ ፊት በወጣች ጊዜ*